ይህ መመርያ ለሂደቱ በምን መልኩ እንደሚዘጋጁ፣ ወደ ሆስፒታሉ ወይ የቀዶ ጥገና ማእከል ከመጡ በኋላ ምን እንደሚጠብቁና ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ እንክብካቤዎን በምን መልኩ እንደሚያቅዱ መረጃ ያቀርባል። ተጨማሪ ጥያቄ ካሎት እባክዎትን ቀዶ ጥገና ያካሄደውን ሀኪም ወይም ሂደቱ ከማካሄዶ በፊት ቃለ መጠይቅ ያደረገሎት የእንክብካቤ ቡድን ያነጋግሩ።

## በዚህ ሰነድ ውስጥ የሚያገኙት


1. የመጀመርያ እርምጃዎ
2. ለቅድመ-ቀዶ ጥገና ግምገማ መዘጋጀት፡ ምን ይጠብቁ
3. ቀዶ ጥገና ከማካሄዶ በፊት ማድረግ ያለቦት ጠቃሚ መመርያ፡ ምን ማወቅና ምን ማምጣት አለቦት
4. የመፆም መመርያ
5. የቀድሞ ቀዶ ጥገና የቆዳ ዝግጅት መመርያዎች
6. የማገገምና ወደ ቤት መሄድ
7. የቀዶ ጥገና ሒሳቦችና ክፍያያዎች መረዳት
8. ቦታና ዝርዝር አድራሻ

## 1. የመጀመርያ እርምጃዎ

ለሂደቱ ቀጠሮ ካስያዙ በኋላ፣ እባክዎትን ወደ MyChart በ **inova.org/mychart** በመግባት **ኦንላይን የህክምና ታሪክ መጠይቅ ኦንላይን ይሙሉ**፡፡

አዲስ ተጠቃሚ ከሆኑና MyChart ከሌሎት፣ እባክዎትን በ **inova.org/mychart** **አሁን ይመዝገቡ**፡፡ በ MyChart ቴክኒካዊ ችግር ካጋጠሞት እባክዎትን በ855-MYINOVA (855-694-6682) በመደወል ተወካዩን ለማናገር ‹‹4›› ይጫኑ፡፡

### ለምን MyChart ከቀዶ ጥገናዎ ወይም ከሂደቱ ጋር አስፈላጊ የሆነው

MyChart ደህንነቱ የተጠበቀ ኦንላይን የጤና መሳሪያ ሲሆን ከቀዶ ጥገና ወይም ከሂደቱ በፊት እና በኋላ ጠቃሚ ነው፡፡ በትክክል እንዲከታተሉ እና ያለችግር እንዲያገግሙ እንዴት እንደሚረዳዎት እነሆ፡

**ከቀዶ ጥገና ወይም ሂደትዎ በፊት**

- ቅድመ ቀዶ ጥገና መመርያዎችን ማግኘት
  መፆምና መድህኒት መመርያ ጨምሮ ለመዘጋጀት የሚያስፈልገትን ነገር ሁሉ ማግኘት፡፡
- የምርመራ ውጤት መመልከት
  ምልክቶች ምስሎችና ግምገማዎች በደረሱበት ጊዜ በአስቸኳይ መመልከት፡፡
- ቀጠሮ ማስተዳደር
  በማንኛውም ሰዓት ቀዶ ጥገና ወይም ሂደት ማረጋገጥ፣ ቀጠሮ መቀየር ወይ ማየት፡፡

**ቀዶ ጥገና ወይ ሂደቱ ከተካሄደ በኋላ**

- የማገገም መረጃ መገምገም
  ሲወጡ ያለውን መመርያ፣ ቁስል ህክምናና መድህኒት ዝርዝር፡፡
- ለእንክብቤ ቡድኖ መልእክት መላክ
  አስቸኳይ ያልሆኑ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሳይደውሉ ምላሽ ያግኙ፡፡
- ያሎትን ለውጥ መከታተል
  ክትትል ለመቀጠልና ማንኛውም ከድሕረ-ቀዶ ጥገና ጋር የተያያዙ ስጋቶችን ሪፖርት ለማድረግ፡፡

እባክዎትን አስተርጓሚ የሚያስፈልጎት ከሆነ ቀጠሮ በሚይዙበት ጊዜ ያሳውቁን፡፡

አብዛኛው ጊዜ ፍላጎቶ ላይ መሰረት በማድረግ በስልክ፣ ቴሌሜዲስን ወይ በአካል ከቀዶ ጥገና በፊት የሚካሄደው ቃለ መጠይቅ አብዛኛው ጊዜ ከ 30 እስከ 90 ደቂቃ ይወስዳል፡፡ አመቺ የሆነ የቀጠሮ ግዜ ለማግኘት እንዲረዳዎት በተቻለ ፍጥነት ቀጠሮ አስቀድመው እንዲይዙ እንመክራለን፡፡

## 2. ለቅድመ-ቀዶ ጥገና ግምገማ መዘጋጀት፡ ምን ይጠብቁ

**ቅደመ ቀዶ ጥገና ግምገማ ከላቁ የልምምድ አቅራቢ ወይም ከቅድመ-ሥርዓት የስልክ ነርስ ጋር በሚያካሂዱበት ጊዜ**

- የህክምና፣ መድሀኒት ታሪኮን መገምገምና ማንኛውንም የሚያስፈልጉ ምርመራዎችን ማካሄድ
- የምርመራ ውጤት መገምገምና ከእንክብካቤ ቡድን ጋር በመሆን ክትትል ማቀናጀት
- ሁሉም Inova ሰነዶችና ተጨማሪ መረጃዎች መሞላታቸውን ማረጋገጥ
- መጾም እና መድሃኒቶችን ጨምሮ የቅድመ ቀዶ ጥገና እና የሂደት መመሪያዎችን ማቅረብ
- ያሎትን ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ መመለስ

**ቅድመ ሂደት ግምገማ ቀጠሮ ቀን፡** ______________________________

**ቅድመ ሂደት ግምገማ ቀጠሮ ሰዓት፡** ______________________________

**ቅድመ ሂደት ግምገማ ቦታ (እባክዎትን አንድ ይምረጡ)**

☐ Inova የቅድመ ቀዶ ጥገና ግምገማዎች – Alexandria
4320 Seminary Rd.
Alexandria, VA 22304
ስልክ፡ 703-504-7880

☐ Inova የቅድመ ቀዶ ጥገና ግምገማዎች – Willow Oaks (Fairfax)
8260 Willow Oaks Corporate Dr. #650
Fairfax, VA 22031
ስልክ፡ 703-776-2000

☐ Inova የቅድመ ቀዶ ጥገና ግምገማዎች – Fair Oaks
3700 Joseph Siewick Dr., #100
Fairfax, VA 22033
ስልክ፡ 703-391-4809

☐ Inova የቅድመ ቀዶ ጥገና ግምገማዎች – Loudoun
44045 Riverside Pkwy. #165
Leesburg, VA 20176
ስልክ፡ 703-858-8192

☐ Inova የቅድመ ቀዶ ጥገና ግምገማዎች – Mount Vernon
2501 Parkers Ln.
Alexandria, VA 22306
ስልክ፡ 703-664-7545

## 3. ቀዶ ጥገና ከማካሄዶ በፊት ማድረግ ያለቦት ጠቃሚ መመርያ፡ ምን ማወቅና ምን ማምጣት አለቦት

1. **ደህንነትና መጓጓዣ**
   - **ወደ ቤት ለማጓጓዝ ዝግጅት ማድረግ፡፡** ለእርስዎ ደህንነት ሲባል ማደንዘኛ ከወሰዱ በኋላ መኪና መንዳት ወይ የህዝብ መጓጓዣ እንዲጠቀሙ አይፈቀድም፡፡ ሀላፊነት የሚሰማው አዋቂ ከእርስዎ ጋር ሊሆን **ይገባል**፡፡ የህዝብ መጓጓዣ ወይ ራይድሼር የሚጠቀሙ ከሆነ **ከመኪና ሹፌሩ ውጪ** ሌላ አዋቂ ከእርስዎ ጋር መሆን አለበት፡፡
     ቀዶ ጥገና ከተካሄደ የመጀመርያ 24 ሰዓት ውስጥ የሆነ ሰው ከእርስዎ ጋር እንዲሆን አጥብቀን እንመክራለን፡፡
   - **ታካሚው ከእንክብካቤ ጋር የተያያዘ ውሳኔ መወሰን የማይችሉ ከሆነ** አዋቂ ከጎናቸው ሊሆንና ያሉትን የፈቃድ ቅፆችን መሙላት ይኖርበታል፡፡
   - **እባክዎትን አስቀድመው ልጆትን የሚጠብቅሎት ሰው ያዘጋጁ፡፡** ልጆች ራሳቸው ታካሚዎች ካልሆኑ በስተቀር ቀዶ ጥገና በሚካሄድበት ስፍራ እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም፡፡ ሂደቱ በሚካሄድበት ስፍራ አንድ የቤተሰብ አባል ብቻ ከእርስዎ ጋር ይሆናል፡፡ እባክዎትን ሂደቱ በሚካሄድበት ወቅት የሚጠይቆትን ጠያቂ ቁጥር ይገድቡ፡፡ ጉንፋን ወረርሽኝ በሚከሰትበት ጊዜ ተጨማሪ ገደቦች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

2. **ቁጠሮና ሕመም**
   - **ቀጠሮ ለመቀየር ወይም ሂደቱን ለመሰረዝ በተቻለ መጠን በፍጥት ቀዶ ጥገና ሀኪሞን ያግኙ፡፡**
   - **ሂደቱ ከመካሄዱ በፊት ከታመሙ ወይም ትኩሳት ካሎት በአስቸኳይ ወደ ቀዶ ጥገና ሀኪሞ ጋር ይደውሉ፡፡** እባክዎትን እነሱን ለማሳወቅ ቀዶ ጥገና እስከ ሚካሄድበት ቀን አይቆዩ፡፡

3. **ምን ይዘው ይምጡ**
   - ሕጋዊ **መታወቅያ፣ የመድህን ካርድ፣ ፋርማሲ ካርድ** እና **ክፍያ የሚከፍሉበት መንገድ** (ቼክ፣ ጥሬ ገንዘብ ወይም ክሬዲት ካርድ)፡፡
   - ካሎት **አስቀድሞ የሚሰጥ መመርያ፣ ኑዛዜ** ወይም **ሕጋዊ ውክልና** ቅጂ ይዘው ይምጡ፡፡ ሁሉም ታካሚዎች አስቀድሞ የሚሰጥ መመርያ እንዲኖራቸው እናበረታታለን፡፡ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት inova.org/advancedirective ይጎብኙ፡፡
   - **የጆሮ ማዳመጫ -** የእርስዎ ስምና የትውልድ ዘመን ያለበትን ማስቀመጫ ይዘው ይምጡ፡፡
   - **መነፅር -** ማስቀመጫ ይዘው ይምጡ፡፡ እባክዎትን **ኮንታክት ሌንስ እቤትዎ ያስቀምጡት**፡፡
   - **CPAP ወይም BiPAP ማሽን** የሚጠቀሙ ከሆነና ተከታትለው ሂደቱን ለማካሄድ ቀጠሮ ካሎት ይዘዋቸው ይምጡ፡፡ ወደ ሆስፒታሉ የሚገቡ ከሆነ Inova ጊዝያዊ ክፍል የምናዘጋጅሎት ይሆናል፡፡

4. **ቅድመ ቀዶ ጥገና ቆዳና ንፅህና ዝግጅት**
   - በቀዶ ጥገና ሐኪምዎ ወይም በቅድመ-ጥገና አቅራቢዎ ካልታዘዙ ካልሆነ በስተቀር **በገጽ 7 ላይ ያለውን የቆዳ ዝግጅት መመሪያ ይከተሉ**፡፡
   - ቀዶ ጥገና ከማድረግዎ በፊት **ባሉት 24 ሰዓታት** አይላጩ ወይ **ጸጉርዎ አያስወግዱ**፡፡
   - ሂደቱ በሚካሄድበት ጊዜ ሎሽን፣ ሽቶ፣ የሚቀቡ ምርቶች ወይ ሜከአፕ **መቀባት የለቦትም**፡፡

5. **ምን ይለብሳሉ**
   - **ሰፋ ያሉና ምቹ ልብሶችን** ይልበሱ፡፡
   - **ሁሉንም ጠቃሚ ነገሮችና ጌጣጌጦች በቤትዎ ውስጥ ያስቀምጡ፡፡** ከመምጣቶ በፊት ሁሉንም **ቀለበትና ጌጦችን** ያውልቁ፡፡

6. **መድሀኒት መመርያዎች**
   - ለደህንነትዎ ሲባል **በሚቆዩበት ጊዜ በሆስፒታል እንክብካቤ ቡድንዎ የተፈቀዱ መድሃኒቶች ብቻ ጥቅም ላይ ሊውሉ** ይችላሉ፡፡ ይህ ሁሉንም ያለሀኪም የሚገዙ መድሃኒቶችን ያጠቃልላል ለምሳሌ aspirin፣ acetaminophen፣ ibuprofen፣ Zyrtec፣ Claritin፣ የአስም መድሀኒት ወዘተ፡፡
   - **የውጭ መድሃቶች** በ Inova በሚቆዩበት ወቅት በሚሰጥዎት ከሚታዘዝልዎት መድሃኒት ጋር **ጎጂ ችግሮች ሊያስከትሉ የሚችሉ ሲሆን፡፡**
   - አስፈላጊ ከሆነ ለቀዶ ጥገና በሚመጡበት ጊዜ የመድሃኒት ጠርሙሶች ይዘው ከምምጣት ይልቅ **እባክዎ የታዘዘልዎትን መድሃኒቶች** ይዘው ይምጡ፡፡

## 4. የመፆም መመርያ

የህክምና ሂደትዎ በአንስቲዢያ ወይ ሴዳሽን የሚካሄድ መሆኑ መመርያዎቹን በጥንቃቄ ይከታተሉ፡፡ እነዚህን መመርያዎች አለመከተል የችግርን የመወሳሰብ አጋጣሚን እንዲጨምር እና ቀዶ ጥገናውን እንዲዘረዝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**ጠቃሚ ምክሮች፡**

- የቀዶ ጥገና ሃኪምዎ ወይም የሂደት ባለሙያዎ ከላይ ከተጠቀሱት የሚለዩ ልዩ የአመጋገብ መመሪያዎችን ከሰጥዎት ሁል ጊዜ በጣም ጥብቅ የሆነውን መመሪያ ይተግብሩ፡፡
- ለስኳር ወይ ክብደት ለመቀነስ **Wegovy፣ Ozempic፣ Mounjaro ወይ Zepbound የመሳሰሉ GLP-1 መድህኒት የሚወስዱ ከሆነ** ቀዶ ጥገና ከማካሄዶ ከ24 ሰዓት በፊት ምንም ዓይነት ደረቅ ምግብ ወይ ንፁህ አለመውሰዶ አስፈላጊ ነው፡፡
- እኒዘህን የጾም መመርያዎች አለመከተል ሂደቱን የማወሳሰብ ደረጃ እንዲጨምርና ህክምናዎን እንዲሰረዝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**መደበኛ የጾም መርሃ ግብሮች**

| የሚዋጡ ነገሮች | ጾም ማቆም አስፈላጊ የሚሆንባቸው ጊዜያት |
|---|---|
| ንጹህ መጠጦች | ቀዶ ጥገናውን ለማድረግ ከተያዘው ጊዜ 2 ሰዓታት ቀደም ብሎ |
| የእናት ጡት ወተት | ቀዶ ጥገናውን ለማድረግ ከተያዘው ጊዜ 4 ሰዓታት ቀደም ብሎ |
| የጨቅላ ህጻናት ፎርሙላ | ቀዶ ጥገናውን ለማድረግ ከተያዘው ጊዜ 6 ሰዓታት ቀደም ብሎ |
| የሰው ያልሆነ ወተት | ቀዶ ጥገናውን ለማድረግ ከተያዘው ጊዜ 6 ሰዓታት ቀደም ብሎ |
| ደረቅ ምግቦች | ቀዶ ጥገናውን በሚያደርጉበት ምሽት ከ 11 ፒኤም በኃላ ደረቅ ምግብ አለመመገብ |

**GLP-1 RAs ለሚወስዱ የማይመገብዋቸው ምግቦች**

| የሚዋጡ ነገሮች | ጾም ማቆም አስፈላጊ የሚሆንባቸው ጊዜያት |
|---|---|
| ንጹህ መጠጦች | ቀዶ ጥገናውን ለማድረግ ከተያዘው ጊዜ 4 ሰዓታት ቀደም ብሎ |
| ከፍተኛ የካርቦሃይድሬት ያላቸው ፈሳሾች (ይህ ማለት ClearFast) | ቀዶ ጥገናውን ለማድረግ ከተያዘው ጊዜ 8 ሰዓታት ቀደም ብሎ |
| የሰው ያልሆነ ወተት | ቀዶ ጥገናውን ለማድረግ ከተያዘው ጊዜ 24 ሰዓታት ቀደም ብሎ |
| ደረቅ ምግቦች | ቀዶ ጥገና ከሚያደርጉበት ጊዜ በፊት ባሉት 24 ሰዓታት ደረቀቅ ምግብ አይመገቡ |

**ሆዳቸው ባዶ ለማድረግ መዘግየት ለሚታይባቸው የጾም መስፈርቶች**

| የሚዋጡ ነገሮች | ጾም ማቆም አስፈላጊ የሚሆንባቸው ጊዜያት |
|---|---|
| ንጹህ መጠጦች | ቀዶ ጥገናውን ለማድረግ ከተያዘው ጊዜ 4 ሰዓታት ቀደም ብሎ |
| ከውሃ ውጭ ያሉ ፈሳሾችና ደረቅ ምግቦች | ቀዶ ጥገናውን ለማድረግ ከተያዘው ጊዜ 24 ሰዓታት ቀደም ብሎ |
| ከታቀደው ሂደት 48 ሰአታት *በፊት* ታካሚዎች ዝቅተኛ ቅባት እና ዝቅተኛ ቅሪት አመጋገብ እንዲጀምሩ ታዝዘዋል | |

## 5. የቀድሞ ቀዶ ጥገና የቆዳ ዝግጅት መመርያዎች

የኢንፌክሽን አደጋን ለመከላከል ከቀዶ ጥገኛ በፊት ቆዳዎ ክሎሮክሳይድ ግሉኮንት *(Chlorhexidine Gluconate (CHG))*፣ 4%, በተባለ ጀርም ገዳይ ውሁድ ይታጠቡ፡፡

**ከ CHG የት ይገኛል**
በመድሃኒት መሸጫ ይገኛል-ማዘዣ አያስፈልግም፡፡ በአብዛኞቹ በአከባቢው የሚገኙ ፋርማሲዎች ይገኛል፡፡ ድጋፍ ከፈለጉ የፋርማሲ ባለሙያውን ይጠይቁ፡፡

**የተለመዱ ብራንድ ስሞች፡**
*Hibiclens፣ Hibistat፣ Exidine፣ Hex-A-Clens*

**በአማካይ አንድ ጊዜ** ለመታጠብ ከ**2-4 አንስ CHG** ያስፈልግዎታል፡፡

**CHG መቼ ይወስዳሉ**
**ለአብዛኛወቹ ቀዶ ጥገኛዎች፡**

- **ሁለት ጊዜ** ይታጠቡ፡
  - አንዱ ቀደም ብሎ **ከቀዶ ጥገና ሌሊት**
  - አንዱ በቀዶ ጥገናው **ጥዋት**

**ለአከርካሪ አጥንት ወይም ለጋራ ምትክ ቀዶ ጥገና፡**

- **ሶስት ጊዜ** ይታጠቡ፡
  - አንዱ **በእያንዳንዱ በቀዶ ጥገና ሁለት ሌሊት ቀደም ብሎ** ወይ በቀዶ ጥጥና ወቅት
  - አንዱ በቀዶ ጥገና **ጠዋት** ወይ በቀዶ ጥገና ወቅት

**CHG ውሁድ እንዴት ይጠቀማሉ**

1. በተለመደው ሳሙና እና ሻምፑ ይታጠቡ፡፡
2. በሚገባ ይለቅለቁ፡፡
3. ውሃውን ይዝጉት፡፡ CHG በእጅዎ ይቀቡት(የእቃ ማጠቢያ ወይም ስፖንጅ አይደለም)፡፡
   - **ፊትዎ፣ ጸጉርዎ እና የመራብያ አካላትዎ አይንኩ፡፡**
4. መላውን ሰውነትዎን በተለይም ቀዶ ጥገና በተደረገበት አካባቢ - ለ **3 ደቂቃዎች** ቀስ ብለው ይሹት፡፡
   - እገዛ አስፈላጊ ከሆነ ረዳቱ በመጀመሪያ እጃቸውን በደንብ መታጠብ አለበት፡፡
5. CHG ሙሉ በሙሉ ይለቅልቁት፡፡
6. በንጹህ **ፎጣ ያድርቁት**፡፡
7. ሎሽን፣ ዶድራንት፣ ፓውደር ወይ ሽቶ **አይጠቀሙ፡፡**
8. ንጹህ **ፒጃማ ወይ ልብስ** ይልበሱ፡፡
9. በ CHG ታጠቡ በኃላ **ከቤት እንስሳት የቅርብ ንክኪ ያስወግዱ**፤ እንስሳቱ ባክተርያ ሊያስተላልፉ ችላሉ፡፡
10. ቀዶ ጥገና ባደረጉበት ጠዋተ እነዚህን ሂደቶች ይድገሙ— መደበኛ ሳሙናና ሻምፖ **አይጠቀሙ**፡፡ **CHG ብቻ** ይጠቀሙ፡፡

**የጸጉር ማስወገድ መመርያዎች**

- ቀዶ **ጥገናውን ካደረጉ በኃላ ባሉት 24 ሰዓታት** ጸጉርዎን አይላጩ ወይም ጸጉር የማስወገጃ ዕቃዎች **አይጠቀሙ-** CHG አዲስ ለታለጨ ጸጉር ሊያስከክ ይችላል፡፡
- መላጨት አስፈላጊ ከሆነ **CHG ከመጠቀምዎ በፊት** እና ቀዶ ጥገና ከማድረግዎ **በፊት ባሉት 24 ሰዓታት** ይላጩ፡፡
- አስፈላጊ ከሆነ የቀዶ ጥገና ቡድንዎ በቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ ማንኛውንም የፀጉር ማስወገጃ ያካሂዳል፡፡

**CHG የደህንነት ምክሮች**

- CHG በፊትዎ፣ ጭንቅላትዎ እና መራብያ አካላቶ አይጠቀሙ፡፡
- CHG **በመታጠቢያው ውስጥ ብቻ** ይጠቀሙ፡፡ ገላውን መታጠብ የማይቻል ከሆነ አማራጭ መመሪያዎችን ለማግኘት የቀዶ ጥገና ሃኪምዎን ያነጋግሩ፡፡
- የመቅላት፣ ሽፍታ ወይም የቆዳ መቆጣት ካስተዋሉ CHG መጠቀምዎን በማቆም **የቀዶ ጥገና ሃኪምዎን ያነጋግሩ**፡፡

## 6. የማገገምና ወደ ቤት መሄድ

- አማካኝ የማገገምያ ግዜ በተለምዶ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ነው፣ ነገር ግን በሚካሄደው ሂደትና የሚኖረው የጎንዮሽ ችግር መሰረት በማድረግ ሊረዝም ይችላል፡፡
- ከመውጣቱ በፊት እርስዎ እና ተንከባካቢዎ ከቀዶ ሐኪምዎ መመሪያዎች እና ማዘዣዎች ትቀበላላችሁ፡፡ በቤት ውስጥ ማገገሚያዎን ለመቀጠል በደንብ እንደተዘጋጁ እናረጋግጣለን፡፡
- ሂደቱን ያካሄዱበት ቦታ ፋርማሲ ካለው ከመውጣቶ በፊት የታዘዘሎትን መድሀኒት እዛው ማስሞላት ይችላሉ፡፡
- እንደ ማስታወሻ፣ ለእርስዎ ደህንነት ሲባል ማደንዘዣ ከተሰጦት በኋላ መኪና ሊያሽረክሩ ወይ ብቻዎን የህዝብ መጓጓዣ እንዲጠቀሙ አይፈቀድሎትም፡፡ ኃላፊነት የሚሰማው አዋቂ ከሆስፒታል ወደ ቤትዎ አብሮዎት መሄድ አለበት፡፡ የሕዝብ ማመላለሻ ወይም የተሽከርካሪ አገልግሎት ከተጠቀሙ ከሹፌሩ ውጪ ሌላ አዋቂ ሰው ወደ ቤትዎ የሚሄድ መኖር አለበት፡፡ ሂደቱ ከተካሄደ ለመጀመርያ 24 ሰዓት አዋቂ ከእርስዎ ጋር እንዲኖር አጥበቀን እንመክራለን፡፡

## 7. የቀዶ ጥገና ሒሳቦችና ክፍዎያዎች መረዳት

ቀዶ ጥገና ከማድረግዎ በፊት የ Inova የሒሳብ አገልግሎት ክፍል የሚነግርዎት፡

- ያሉት ሽፋኖችና ጥቅሞች
- ከኢንሽራንስዎ አስፈላጊ ፈቃድ ማግኘት
- የሚኖርብዎት የፋይናንስ ወጪ እንዲገነዘቡ ማገዝ
- ማንኛውንም የፋይናንስ ማስተካካያዎች ማድረግ

እርስዎን ማግኘት ካልቻልን እባክዎ በቀዶ ጥገናዎ ቀን ማንኛውንም ተፈጻሚ የሚሆን የትብብር ክፍያ ወይም የጋራ ክፍያ ለመክፈል ይዘጋጁ፡፡

የኮስሞቲክስ ቀሮ ጥገናዎች ቀደም ብለው መከፈል ይኖርባቸዋል።

**ሂደቱ ከታኬደ በኋላ የተለያዩ ክፍያዎች እንደሚከፍሉ መጠበቅ አለቦት።**

- ከቀዶ ጥገና ወይም ሂደቶ ጋር ለተያያዙ ክፍያዎች የቀዶ ጥገና እንክብካቤ አቅራቢዎ መጀመርያ የመድህን ድርጅቶን የሚያናግር ይሆናል።
- እንደ ተቀናሽ፣ የጋራ ክፍያ ወይም የጋራ መድህን ለመሳሰሉ የቀሩት ክፍያዎች ደግሞ ለእርስዎ ይደርሶታል።
- ከቀዶ ጥገና ቡድኑ የተለያዩ ክፍያ ዝርዝር የሚደርሶት ይሆናል። ይህም የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡

**የሆስፒታል ክፍያዎ፡**

- ይህ ቀዶ ጥገና ወይ ሂደቱ ለተካሄደበት ሆስፒታል ወይ ቀዶ ጥገና ማእከል የሚከፍሉት ክፍያ ነው። ይህ ክፍያ የሰራተኞች፣ አቅርቦትና ለቀዶ ጥገና አገልግሎት የሚውሉ መሳርያ የሚወጣ ወጪ ነው።
- ክፍያ የሚመለከቱ ጥያቄዎች በቀጥታ በክፍያ ላይ የተጠቀሰውን ሆስፒታሉ/ተቋሙ በቀጥታ መጠየቅ ይችላሉ። ወይ ወደ Inova ታካሚዎች የፋይናንስ አገልግሎት በ 571-423-5750 ይደውሉ።
- ግምት በተመለከተ ጥያቄ ካሎት እባክዎትን ሂደቱ ወደ እሚካሄድበት ቦታ ይደውሉ። የቡድን አባላችን ከሰኞ- ዓርብ ከ 8፡30 ኤኤም እስከ 4፡30 ፒኤም ለእርስዎ ድጋፍ ያደርጋሉ።

**የቀዶ ጥገና ሀኪም ክፍያ፡**

- ይህን የሚመለከት ጥያቄ በክፍያው ላይ የተጠቀሰውን ሀኪም ማነጋገር ይችላሉ።

**የማደንዘዣ ባለሙያ ክፍያ፡**

- በሂደቱ ወቅት ለሚሰጦት ማደንዘዣ የሚመለከቱ ጥያቄዎች በክፍያው ላይ ለተጠቀሰው አንስቴሎጂስት የሚመለከት ይሆናል።
- ከክፍያ ጋር ለተያያዙ ጥያቄዎች በክፍያ ዝርዝር ውስጥ በግልፅ የተዘረዘሩትን አንስትዮሎጂስት ቡድን ያነጋግሩ።

ሂደቱ በሚካሄድበት በ48 ሰዓት ውስጥ ጉንፋን፣ ትኩሳት፣ የማያቋርጥ ሳል ወይም ኢንፌክሽን ካጋጠሞት ለእርስዎ ደህንነት ሲባል ሂደቱን መሰረዝ አለብን። ከተጠራጠሩ ደግሞ እባክዎትን የሚኖሮት ማንኛውም አጠራጣሪ ምልክት በተመለከተ ከሀኪሞ ጋር ይወያዩ።

## 8. ቦታና ዝርዝር አድራሻ

**Alexandria አካባቢ**

**[Inova Alexandria Hospital Surgery Center]**
4320 Seminary Road
Alexandria, VA 22304
703-504-3000
ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎትን www.inova.org/locations/inova-alexandria-hospital-surgery-center ይጎብኙ፡፡

**Inova Mount Vernon Hospital Surgery Center**
2501 Parkers Lane
Alexandria, VA 22306
703-664-7000
ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎትን www.inova.org/locations/inova-mount-vernon-hospital-surgery-center ይጎብኙ

---

**Annandale / Falls Church / Fairfax (Inova Fairfax Medical Campus)**

**Inova Woodburn Surgery Center**
3289 Woodburn Rd, #130
Annandale, VA 22003
571-472-7030
ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎትን www.inova.org/locations/inova-woodburn-surgery-center ይጎብኙ፡፡

**Inova Fairfax Hospital Surgery Center**
Inova Fairfax Medical Campus
3300 Gallows Road
Falls Church, VA 22042
703-776-5900
ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎትን www.inova.org/locations/inova-fairfax-hospital-outpatient-surgery-center ይጎብኙ፡፡

**[Inova Professional Services Building – Surgery Center](www.inova.org/ifmc/psb-sugery)**
Inova Fairfax Medical Campus
3300 Gallows Road
Falls Church, VA 22042
📞 703-776-6630
ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎትን www.inova.org/ifmc/psb-sugery ይጎብኙ፡፡

**Inova Saville Cancer Screening and Prevention Center**
8081 Innovation Park Dr, Pavilion - Level P1
Fairfax, VA 22031
📞 571-472-3500
ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎትን www.inova.org/locations/inova-saville-cancer-screening-and-prevention-center ይጎብኙ

---

### Fair Oaks አካባቢ

**Inova Fair Oaks Hospital Surgery Center**
3600 Joseph Siewick Drive
Fairfax, VA 22033
📞 703-391-3600
ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎትን www.inova.org/locations/inova-fair-oaks-hospital-surgery-center ይጎብኙ

---

### Leesburg / Loudoun አካባቢ

**Inova Loudoun Hospital Surgery Center**
44045 Riverside Pkwy
Leesburg, VA 20176
📞 703-858-6490
ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎትን www.inova.org/locations/inova-loudoun-hospital-surgery-centers ይጎብኙ